ሕይወት አስተማረችኝ

ዱንያ ላይ ይህን ያህል ኖሬ ካልተማርኩማ ምኑን ሰው ሆንኩ ታዲያ! ... የሰው ልጅ አንድም በፊደል "ሀ" ብሎ አሊያም በመከራ "ዋ" ብሎ ይማራል ይባል የለ!!። ዱንያ መከራዋን አጥብታ ካሳደገቻቸው ሰዎች አንዱ ነኝ። በዱንያ ላይ ቆይታዬ ከተማርኳቸው ነገሮች መካከል የተወሰኑትን ላስታውሳችሁ... የማስታውሰው ራሴንም እናንተንም ነው።

፩- ለድካም ራስህን አዘጋጅ

በአንድ ወቅት ከአንድ ወዳጄ ጋር ሰፈር ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ እያለን የአንድ ጓደኛውን ህፃን ልጅ መንገድ ላይ ተመለከተና አነሳው። ከዚያም አግላብጦ ሳመውና እንደ ቀልድ አንዲህ አለው- "አቤት እኛ የደረስንበት ቦታ ለመድረስ የሚጠብቅህ ልፋትና ድካም!... ኬጂ የሚባል አለ፤ ከዚያ ኤሌመንተሪ፣ ከዚያ ሃይስኩል፣ ከዚያ ዩኒቨርስቲ፣ ከዚያ ሥራ ፍለጋ፣ ከዚያ ትዳር ፍለጋ... እያለ ብዙ ቆጠረለት።

በንግግሩ እንደው እንደዋዛ በዚህ ዕድሜዬ የመጣሁበትን መንገድ መለስ ብዬ አሰላሰልኩ። ድካሙና ጉዞው ገዝፎ ታየኝ። በልጅነት ነበር ከቤት የወጣሁት። የደረስነትን ሕይወት እስኪበቃኝ አይቼዋለሁ። በመንገዱም ብዙ ተቸግሬያለሁ። በትምህርት ዓለም ብዙ ወድቄ ተነስቻለሁ። ላጤነትን እስከ ጥግ ድረስ ኖሬበታለሁ። አሁንም ቢሆን የዱንያ ፈተናዋ እንዳለ ነው።

አርግጥ ነው የኔ ሕይወት ከሌላው የሰው ልጅ ሕይወት የተለየ ነው ብዬ አላስብም። ዱንያ ሌላውን አፈር እንዳበላችው ሁሉ እኔንም አፈር ደቼ አብልታ አሳድጋኛለች። በልምጭ ለምጣን ገርፋ እዚህ አድርሳኛለች። እስከመቃበር አፋፍ ድረስ አሁንም ግርፊያዋ ይቀጥላል፤ አይቆምም። አሷ በዕድሜ ከፍ ብሷል ብላ አርጩሜዋን አታወርድም።

ሁሌም መርሳት የሌለብኝን አንድ ነገር ለኔም ለናንተም ላስታውስ። ዱንያ ከማስበውና ከምታስቡት በላይ የድካም አገር ናት። አላህም እሱን እስከምንገናኘው ድረስ እንደምንደክም ነግሮናል። ስለዚህም እኛም ይህች አገር አድካሚ መሆኗን አውቀን ባህሪዋን ተገንዝበን ልንኖራት ይገባል። በሷ ላይ እስካሉ ድረስ ዕረፍት አይታሰብም። ወደ ውሃ ተገብቶ ቀዘቀዘኝ አይባልም።

ዱንያ በአንድ ብቻ ሳይሆን በብዙ ነገር ታደከማለች። በኑሮ ራሳችንን ለመለወጥ በምናደርገው ጥረት ታደከመናለች፤ በሊማን ለመሻሻል በምናደርገው ትግል ታደከመናለች፤ በትምህርት ለማደግ፣ በሥነምግባር ከፍ ለማለት... እነኚህ ሁሉ በነፃ የሚገኙ አይደሉም። ያደከማሉ። ድካመ ደግሞ የአንድ ሰሞን ብቻ አይደለም፤ የዕድሜ ልክ ነው።

የሰው ልጅ ሆይ! አንግዲያውስ ቁርጥህን እወቅ። ዱንያ ላይ እስካሉ ድረስ ምንም ዕረፍት የለም። ዱንያ በየቀኑ የምታቀርብልን አጀንዳ አላት። መደፈን የሚገባው ከፍተት አላት። የዕለት አጀንዳዋን ለመዝጋትና ከፍተቷንም ለመሙላት ከጧት እስከ ማታ፣ ከማለዳ እስከ ምሽት፣ ከልጅነት እስከ ዕውቀት፣ ከሕይወት እስከ ህልፈት ትደከማለህ... ትደከማለህ... ትደከማለህ...! በመጨረሻም ከጌታህ ጋር ትገናኛለህ። በምድር ላይ ስላሳለፍከው ሕይወትም ትመረመራለህ።

በአላህ ፈቃድ ዱንያ ላይ እንድትገኝ የተደረግከው የሰው ልጅ ሆይ! በዕድሜ ቁጥር ከታች፣ ከመካከልም ሆነ ከላይ ያለኸው ሰው ሆይ!... ዱንያ ውሰጥ ስትኖር፤ ያሰብካቸውን ነገሮች በቀላሉ ልታሳካ እንደማትችል ከወዲሁ እወቅ። እንደምትደክም እና ድካምህም ከባድ እንደሆነ አስቀድመህ ተገንዘብ። ለከባድ ድካምም ራስህን አዘጋጅ። ዱንያ ቀልድ አታውቅም።

2- ከሰዎች ምላስ አትተርፍም

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ካካሄዷቸው ዘመቻዎች መካከል የተቡክ ዘመቻ ከባዱ እንደሆነ ይነገራል። ከባድ ነው ካስባሉት ነገሮች መካከል- የሚዘምቱበት አገር በጣም ሩቅ መሆኑ፣ ዘመቻውም እጅግ ሞቃታማ በሆነ ሐሩር ወቅት ላይ ሊደረግ መታሰቡ እና የሚገጥሙት የጠላት ጦርም በቁጥር እጅግ ብዙ እጥፍ የሚበልጣቸው መሆኑ ይጠቀሳል።

ለዚህም ሲባል የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦቻቸው ለዘመቻው በከብደቱ ልክ እንዲዘጋጁ አሳሰቡ። ሁሉም ሰው ለሙስሊሙ ጦር ስንቅ ይሆን ዘንድ ያለውን ያህል በአቅሙ እንዲያዋጣም አዘዙ። በዚህን ጊዜ ሰዎች ሁሉ ያላቸውን አዋጡ። በነፍስ ወከፍ ከቁና ተምር እስከ ለበርካታ ሶሐቦች ሊውል የሚችል ትጥቅና ስንቅ ለገሱ። ግና በሰዎች መካከል በሰው ልጅ ተቆጣጣሪ ተደርገው የተሾሙ የሚመስሉ ሙናፊቆች ነበሩ። በርግጥ ከሙናፊቅ ምላስ መዳን አይታሰብም። ሙናፊቆቹ፤ ትንሽም ሆነ ብዙ

የሠጡትን አማኞች አላተረፏቸውም። ቁና ተምር የሠጠውን 'አላህ ከዚህ ተምር ሓጃ የለውም' ብለው አጣጣሉ። ብዙ የለገሰውን ደግሞ 'ለይዩልኝና ይስሙልኝ ብሎ ነው ይህን ያደረገው' አሉ።

የሰው ምላስ እንዲህ ነው። በግራ ሁን በቀኝ፣ ከታችም ሁን ከላይ... ከሰው ምላስ አትተርፍም። ምላሰኞች ያለርህራሄ ያጭዱሃል። ያልፋሃል ብለህ አትጠብቅ፤ ሊርምሩህም። ከፍ አለከም ዝቅ፣ ግድ የላቸውም፤ አይለቁህም። ጥሩም ሠራህ መጥፎ ነገር፣ ከሰዎች ምላስ አትተርፍም፤ ከአሳማሚ ንክሻቸው አትድንም። ደግሞ ሁን ከፉ፣ ሙቹም ቢሆን አታመልጥም። ኸይረኛም ሁን ሸረኛ፣ ሰዎች ሙቹም ቢሆን አያፋቱህም። ብትፈልግም ባትፈልግም፣ ብትወድም ባትወድም ይከተሉሃል፤ ይከታተሉሃል። እንደተከተሉህ ትኖራለህ፤ እንደተከታተሉህ ትሞታለህ። ይህንን ከወዲሁ አሳምረህ እወቅ። አንድ ነገር ለመሥራት ካሰብክ፣ በዚያው አግረመንገድህን የሆነ ነገር ለመባልም ተዘጋጅ።

ዛሬ ላይ ደግሞ የሚዲያ ዓይነቶች ከመብዛታቸውና፣ የወሬ ሱስም እጅግ ከመስፋፋቱ ጋር፣ የሰው ሥም ቀላልና ተራ ነገር ሆኗል። ብዙዎች "አላህን መፍራት" የሚባል ነገር ትተዋል። በተለይ ታዋቂ እና ከፊት ከሆንክ ሰዎች ያለአንዳች ይሉኝታ ስላጉት ጉዳይ ከምንም ፈጥረው ያወራሉ፣ የማያውቁትን ያቦካሉ፣ ይዋሻሉ፣ ይቀጥፋሉ። ያላንዳች ይሉኝታ ሥምህን ያጠፋሉ። ይህ ሁኔታቸው የተለመደና 'ምንም ነገር' ሆኗልና ባልጠበቅከውና ባላሰብከው መልኩ፣ በሌለህበት ነገር ሁሉ ሥምህን ቢያነሱ በዚህን ጊዜ አትደናገጥ።

አዎን የሆነ ነገር ለመሥራት ስትዘጋጅ ለሰው ምላስም ሥጋህን አዘጋጅ። ከፍ ባልክ ቁጥር ለብዙዎች ትታያለህ፤ አናት ሆነሃል ማለት ነው። ድንጋይ ያነሳ ሁሉ ወደ አናት ሲወረውር የምናየው ለዚሁ ነው። ወጥተህ ስለምትታይ ያገኙትን ሁሉ እያነሱ ይወረውሩብሃል።

የሰው ልጅ ምድር ላይ ሲኖር ከገንዘቡ ይሁን ከሥጋው የሚከፍለው ግብር ይኖራል። በሰዎች መካከል ከፍ ስትል በሀሜትና በሥም ማጥፋት በሚደርስብህ ቡጨቃ ከከብርህ ግብር ትከፍላለህ። ዱንያ ላይ ሁለት ወዶ አይታሰብም። ከፍ ብለህም፣ ዝምበሉ ብለህም አትችልም።

ስለሆነም ለሰው ምላስ ብዙም ልንጨነቅ አይገባም። ይህ ዓለም ከጥንት ጀምሮ የመጣችበት መንገድ ነውና። አይደለም እንኳን በኛ በተራዎቹ ሰዎች፣ በታላላቆቹ ነቢያትና ደጋግ የአላህ ባሮች ላይ ተቀጥፏል። ነቢዩ ዒሳ (ዐ.ሰ.) ተዋሽቶባቸዋል፤ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ተቀጥፎባቸዋል። ንጽህት ቅድስት መርየም (ዐለይሃ ሰላም) በሰዎች ምላስ ከፉኛ ቆስላለች፤ ዝሙተኛ ተብላለች። ለአናታችን ዓኢሻም (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ምላስ አልቀረም፤ ባልሠሩት ሥራ ሥማቸው ጠፍቷል። ታዲያ ባንተ/ባንቺ፣ በኔ ላይ ቢቀጠፍ ስለምን ይገርምሃል?! ስለምን ይገርምሻል!። ምናልባት ጉዳቱ ከከፋብህ እንኳ ራስህን በራስህ ጠግን፤ ቁስልህን በእጅህ አከም። መጎዳትህንም ለማንም አትናገር።

እናም የሚሻለው ነገር ከእንቅስቃሴያችን ኋላ ሁሉ የሰው ምላስ የተለመደ መሆን ማወቅና መጠበቅ ነው። ቢቀጠፍብህ አትናደድ፤ ሰቀህ አለፍ። ቢወራብህ ጆሮ አትስጥ፤ ተወራብኝ ብለህ አትበሳጭ። ተራ ወሬ ጆሮ ሰጥተህ አታዳምጥ፤ ነገር አታላምጥ፤ ንቀህና ትተህ አለፍ፤ በዓላማህ ቀጥል፤ በመስመርህ ቀጥ በል።

ሰዎች የሆነ ነገር ስላሉና ስላወሩ ከዓላማህ አትመለስ፤ ስለ ንጽሕናህ ሌሎችን ለማሳመንም አትድከም። ባይሆን ወደራስህ ተመለስ፤ ራስህን በብረት አጥር አንጽ። ለሌላ ዙር ሥራ ተዘጋጅ። ራስህን ሁን። ዱንያ ለአሸናፊዎቹና ለብርቱዎቹ ናትና ጠንክር፤ በርታ። በየትኛውም መንገድ ብትጓዝ በመንገድህ ላይ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አትዘንጋ። ሊያስቸግሩህና ሊያደናቅፉህ እንደሚችሉም አትጠራጠር። ይህንኑ አውቀህ ግባበት። የስድብ ቀስቶች፣ የጥላቻ ወንጭፎች፣ የሥም ማጥፋት ፍላፃዎች... እንደሚያገኙህ ተገንዘብ። ከትንሽ ይሁን ትልቅ፣ ከባዳ ይሁን ከዘመድ፣ ከሩቅ ይሁን ከቅርብ፣ ከጠበቅከውም ሆነ ካልጠበቅከው፣ ከማንም ይሁን ከማን፣ ከየትኛውም አቅጣጫ ሊወረወሩብህ ይችላሉ። ካዳመጥካቸው ይጎዱሃል። በተለይ ከጦሩ በላይ የወርዋሪው ማንነት ሊያሳምምህ ይችላል...

ሰዎች ሲሰድቡህና ሲዋሹብህ ቆመህ መልስ መስጠትን አታስበው። እንደ ዳመና ከፍ በል። አዎ ከፍ!። ዳመና የቱን ያህል ቢሰድቡትም ከፍ እንዳለ ይኖራል፣ በጥላው ያጠለናል፣ በውሃም ያረሰርሰናል። አንተም እንደዚያው ሁን። በስድቦች መሃል ከፍ በል፤ በትችቶች መሃል ዝነብ። ያለአንዳች ልዩነት ለሰዎች ሁሉ ጥቀም። ሰዎች ስለ አንድ ነገር ቢናገሩ ስለራሳቸው ሃሳብ እንጂ ስለዚያ ነገር ተጨባጭ አይደለም። ሠራህም አልሠራህ፣ ጠበቅከም አልጠበቅከ በሁሉም ነገር ላይ አስተያየት ከመስጠት ወደኋላ አይሉም። የሰው ሃሳብ ማንነቱን ያንፀባርቃል፤ ውስጡን ይገልፃል እንጂ

የእጉተን ውስጥ ኣይገልጽም። ስለዚህ በትችት መሃል የመሄድ ድፍረት፣ ጉልበትና ልምድ ይኑርህ።

3- ንቀህ ተወው

ለምቶ መቻልና ንቆ መተውን የመሰለ ነገር ይኖር ይሆን!። ዛሬ ላይ የአዋቂ ቁጥር ከማነሱ ጋር አዋቂ ነኝ የሚል ባይ በዝቷል። 'አዋቂ ነኝ' የሚልን ሰው "አዋቂ እኔ ነኝ እንጂ እጉተ ኣይደለህም" ብለህ ቆመህ አትከራከረውም። አዋቂ ነኝ ብሎ ራሱን የቆለለውን መሃይም ማሳመን ከባድ ነው። የቦታዎች ተገቢውን ሰው አለማግኘትና የጃሂል ከፊት መሆን ከቂያማ ምልክቶች መካከል አንዱ መሆኑን አወቅ። ዱንያን አላህ ነውና እንዲህ ያደረጋት አብዝተህ አትገረም። ብዙ አትማረር፤ ተወት አድርገኸው ወደፊት ቀጥል - "አንድ ነገር ባለቤቱ ላልሆነ ሰው የተተወ እንደሆነ ቂያማን ጠብቅ።" ብለዋል ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.)። እናም በዚህ ዓይነቱ ጊዜ ገዘም ብለህ ቂያማን ጠብቅ።

ጃሂል ጋር ተከራክሮ ማሸነፍ ከባድ ነው። አላዋቂን አታውቅም ብሎ ማስረዳት ከንቱ ድካም ነው። ጉዳዩ ለገላጋይም አስቸጋሪ ነው። ዛሬ ላይ የሆነ ጊዜ ድንገት አዋቂ ሰው ጠፍቶ ኢማም እንዲሆን የተደረገ ሰው ከሱ የተሻለ ኢማም መጥቶ ቦታውን አስረከብ ቢባል ኣያስረክብም፤ ሥልጣኑን ልቀቅ ቢባል አይለቅም። ከነአላዋቂነቱ ካልመራሁ ብሎ ሙጭጭ ይላል። ከሱ በላይም አዋቂ እንደሌለ ያስባል። ይህን ሁሉ ትተው ካልሄዱ ዱንያ በየፈርማታው ከትከክለኛ ጉዞአችን ትገታናለች። ከኛ የሚጠበቀው የቻልነውን ያህል ማሳየትና ማድረግ ብቻ ነው።

ወደፊት ብዙ የመራመድ ዓላማ አለኝ ካልክ ንግግራቸው ትከክል እንዳልሆነ የምታውቃቸው ሰዎች ስላንተ ስለሚሉት ነገር ጆሮ አትስጥ። ለመልካም ካልሆነ በስተቀር የሰዎችን ንግግር ከመሬት አታንሳ። ተራ ወሬዎችን እግርህ ሥር ኢድርግ፣ እዚያው በጫማህ እሸውና ከመሬት ደባልቀው። ንቀህ ተወው። እዚያው እሽት እሽት ኢድርገው። ገለባውን ነገር አንስተህ ለዐይንህ አታቅርበው፤ የማይታይን ነገር በማጉሊያ መነጽር እንዲታይ አታድርገው፣ ሕይወት የሌለውን ነገር ነፍስ አትዝራበት፤ የሰው መጥፎ ንግግር ውዳቂ ነውና አቧራውን አራግፈህ ሕይወት አትስጠው። ርካሽ ነውና ዋጋ እንዲያወጣ አታድርገው። ጆሮህን ከማስመታት አሳልፈህ ወደ ልብህ አታድርሰው።

ዱንያ ላይ ዕድሜህን ሊያቃጥሉ ከሚችሉ ነገሮች መካከል አንዱ- ለያንዳንዱ ሰው ለማስረዳት ብለህ የምታጠፋው ጊዜ ነው። ከአንዳንድ ነገሮች አንፃር አይተህ እንዳላየህ፣ ሰምተህ እንዳልሰማህ መሆን ግድ ነው። አንዳንዱም እንደሚያልፍ ጥይት ለጥ ብለህ ተኛ። የተኛ ሰው የሚያየውም ሆነ የሚሰማው ነገር አይኖርም። ቢሰድበትም፣ ቢሙቱትም አያመውም፣ ምንም አይሰማውም። እንቅልፍ ውሰጥ የገባ ሰው ሊናደድም፣ ሊበሳጭም። እንቅልፍ ሌላ ዓለም ነው። እዚያ ዓለም ውሰጥ ስትገባ ሁሉን ነገር ትረሳለህ። ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ሲወስድህ...። ከሰው የምላስ ዱላ እንፃር እንቅልፍ ውስጥ መሆንን የመሰለ ነገር የለም። እንቅልፍን የመሰለ ማሸነፊያ ድል የለም። ችግሩ እንቅልፍ አልወስድህ ካለ ነው። በየምቱ የምትታመም ከሆነ ነው። ስለዚህ ብልህ ሁን፤ ምንም እንዳልተፈጠረ ነገር አድርገህ ተጠቅልለህ ተኛ።

አዎ አንደ አስሓበል ከህፍ ሰዎች ዝም ጭጭ በል። ዋሻው ውስጥ ረጅም እንቅልፍ ተኙና ከእንቅልፋቸው ሲነሱ ድልን ተቀዳጁ። ሲነሱ ያኔ በዘመናቸው ጠላቶቻቸውና አሳዳጆቻቸው የነበሩ ሁሉ ወደ መቃብር ወርደዋል። ሰዎችም ሰለነርሱ ረስተዋል። እነርሱ ግን ዛሬም ድረስ ሕያው ናቸው። አንዳንድ ጊዜ መተኛት ግድ የሚሆንበት ጊዜ አለ። አዎ አንዳንዴ ለወሬዎች ትኩረት ካለመስጠት አንፃር ተኛ አትሰማ፤ ተኛ አትይ፤ ተኛ አትናገር። ማየት የምትፈልገውን ብቻ መርጠህ እይ፤ መናገር የምትፈልገውን መርጠህ ተናገር፤ መስማት የምትፈለግውን መርጠህ ስማ። ካልሆነ ተኛ። ያኔ ሰላም ትሆናለህ። መልስ አትስጥ ሰዎች የሚከተሉት መልስህን ነውና።

4- ለአላህ ብቻ ብለህ ሥራ

ለአላህ ብሎ የሚኖር ሰው ለሰው ግድ አይኖረውም። ለአላህ ብሎ የሚሠራ ሰው የሰው ነገር ትዝ አይለውም። ግንኙነቱ ሁሉ ከአላህ ጋር ነውና። ዱንያ ላይ ስትኖር ኑሮህን ከአላህ አንፃር ኑር። ሥራህንም ስትሠራ ለአላህ ብቻ ብለህ ሥራ። ስለ አላህ ስትኖር አላህ ይወድሃል፤ ሰዎችም ዘንድ ተቀባይነት ይኖርሃል። ስለ ሰው ስትኖር ግን አላህ ይጠላሃል፤ ሰዎችም አንቅረው ይተፉሃል። ሰዎች ስላንተ ያሉትን ያልሆነ ነገር ስታስብ በትችታቸው አትሸማቀቅ፤ በመልካምነትህ ያወደሱህ እንደሆነም በሙገሳቸው አትመክ። በርግጥ የምትሠራው ለአላህ ከሆነ ሁሉን ነገር፤ ኢድናቆቱንም ትችቱንም እኩል አይ። ያኔ መስመር አትለቅም፤ ሚዛን አትስትም፤ ከፍ ትላለህ፤ ንጉስ ትሆናለህ፤ ታሸንፋለህ። ሰው የሚቆመው በጓደኞቹ ብዛት አይደለም፤ ዋስትናና ድህንነት የሚሆነውም ገንዘቡ አይደለም። የሰው ሰላምና ደህንነቱ ከአላህ ዘንድ ነው፤ እሱ